ኢ.ሕ.ባ.ማ
ELA

# የኢንሹራንስ ሕግ

## ዋቢ ሽበሌ ሆቴል

ሚያዝያ 14/2009 ዓ.ም.

**የስብሰባው አጀንዳ፡-** “የኢንሹራንስ ሕግ”

**ጽሑፍ አቅራቢዎች፡-** 1. አቶ ይነበብ ደርሰህ/በኅብረት ኢንሹራንስ ሕግ አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ/

2. አቶ ፋሲል አለማየሁ/የሕግ አማካሪና ጠበቃ እንዲሁም በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የሕግ መምህር የነበሩ/

**አወያይ፡-** አቶ ቢንያም አህመድ/በቅድስት ማርያም ዩኒቨርስቲ መምህር/

**የስብሰባው ቀን፡-** ሚያዝያ 14/2009 ዓ.ም.፣ ከጠዋቱ 2፡30 - 6፡30

**የስብሰባው ቦታ፡-** ዋቢ ሸበሌ ሆቴል

## <u>አቶ ቴዎድሮስ ምህረት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት</u>

የኢንሹራንስ ሕግ ሰፊ መሆኑን እና ውይይቱ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩር አስረድተው አወያዩን አቶ ቢንያም አህመድ እና ጽሑፍ አቅራቢዎችን አቶ ፋሲል አለማየሁን እና አቶ ይነበብ ደርሰህን አስተዋውቀው ውይይቱን ከፍተዋል፡፡

አቶ ይነበብ ደርሰህ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ሀሳቦችን ብቻ እንደሚያነሱ እና ቤቱ ግን በውይይት እንዲያዳብረው ጠይቀው በተለያ 3 ነጥቦች ላይ እንደሚያተኩሩ ገልጸዋል፡፡ እነኚህም፡-

1ኛ/ ኢንሹራብል ኢንተረስት (በኢንሹራንስ ሊሚሸፈን የሚችል ጥቅም)

2ኛ/ የኃላፊነት ኢንሹራንስ እና

3ኛ/ ሠራተኛ እና አካል ላይ የሚደርስ ጉዳት ኢንሹራንስ ናቸው፡፡

## 1ኛ/ <u>ኢንሹራብል ኢንተረስት (በኢንሹራንስ ሊሸፈን የሚችል ጥቅም)</u>

የኢንሹራንስ ክፍያ ለማግኘት የሚያስችል የገንዘብ ወይም የንብረት ጥቅም በሌለበትየኢንሹራንስ ውል ዋጋ ሊኖረው አይችልም፡፡ ወይ የንብረት አለበለዚያም የገንዘብ ጥቅም መኖር አለበት፡፡ ንብረት ወይም ሕጋዊ ሓላፊነት መኖር አለበት፡፡ የገንዘብ ግንኙነት ወይም ንብረት መኖር አለበት፡፡ እንዲሁም ጥቅሙ አሁን መኖር አለበት፡፡ ጥቅሙ ወደፊት የሚጠበቅ ሳይሆን አሁን ያለእና ሕጋዊ መሆን አለበት፡፡ መድን ገቢውጥቅሙ የሚመለከተው ካልሆነ ህጋዊ አይሆንም፡፡ ለምሣሌ አንድ ባለ አክሲዮን የኩባንያው ጥቅም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚነካው ቢሆንም ኩባንያው እራሱን የቻለ የህግ

ሰውነት ስላለው ባለ አክሲዮኑ ሕጋዊ ውክልና ሳይኖረው ስለ ኩባንያው ጥቅም የመድን ውል ለመዋዋል ጥቅሙ አይመለከተውም።

የኢንሹራንስ ሽፋን ዓላማው ጉዳትን ለመቀነስ ነው። ህጋዊ ጥቅም የሌለው ሰው ኢንሹራንስ እንዲገባ ከተፈቀደለት ያንን ንብረት በማጥፋት ካሣ ለማግኘት እንዳይሞክር ያሰጋል። በተጨማሪም ኢንሹራንስ የተጎዳ የሚካስበት እንጂ ያልተጎዳ ሰው የሚወራረድበት ቁማር መሆን የለበትም።

ጥቅሙ ከህግ ወይም ከውል ሊመነጭ ይችላል። ከህግ የሚመነጩት ህይወትና ንብረት ናቸው። ከውል ደግሞ ለምሳሌ አበዳሪና ተበዳሪን መውሰድ ይቻላል። አሰሪና ሰራተኛ ወይም አጓዥና አጋጓዥን ማንሳት ይቻላል።

ሌላው ልብ ሊባል የሚገባው በመርህ ደረጃ ጥቅሙ መኖር ያለበት ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ ነው እንጂ ውሉ በተገባባት ጊዜ አይደለም። ለምሳሌ ንብረት ሲተላለፍ ካሳ የመጠየቅ መብቱም ይተላለፋል። በመሆኑም ካሳ የመጠየቅ መብቱ ከሻጩ ወደ ገዢው የሚተላለፍ በመሆኑ ንብረቱ ከተሸጠ በኋላ በንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ምንም እንኳን የኢንሹራንስ ውሉን የተዋዋለው ሻጩ ቢሆንም አሁን ግን ጥቅሙ ከሻጩ ጋር ስለሌለ የመጠየቅ መብቱ የገዢው ነው ማለት ነው። ሕይወት ግን ሲሆን ጥቅሙ መኖር ያለበት በሚገባበት ጊዜ ነው። ባል ቢሞት ሚስት ጉዳቱ ሲደርስባት ህይወት የለም። ቢሆንም ሚስት ካሣ ክፍያ መጠየቅ ትችላለች።

ሌላው የንግድ ሕግ ቁጥር 675 (1)ዕቃውን ከጉዳት ለመጠበቅ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ኢንሹራንስ ሊያስገባው ይችላል ሲል ይደነግጋል። እንዲሁም የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 ጉዳት እንዳይደርስ በማለት ማንኛውም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ሁሉ ኢንሹራንስ ሊገባለት ይችላል ሲል ይደነግጋል። ቀጥተና ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ኢንሹራንስ ሊገባለት ይችላል የሚለው ሊሰመርበት ይገባል። በሀገራችን ከሚገቡ የመድን ውሎች ውስጥ በአማካይ 65 በመቶ የሞተር ኢንሹራንስ ነው። ብዙ ጊዜ መድን ገቢው መኪና ይሸጥና ገዢው ለመድን ሰጪው (ለኢንሹራንስ ኩባንያው) ሳያሳውቅ ይቀራል። በመድን ፖሊሲዎች ላይ ግን ገዢው ለመድን ሰጪው ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ ውሉ እንደሚቋረጥ ይገለጻል። በንግድ ህግ ቁጥር 673 (1) ላይ ግን ኢንሹራንስ የተደረገለት ነገር ለሌላ በተላለፈ ጊዜ ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም እንኳን የኢንሹራንሱ ውል በሙሉ መብት ለተላለፈለት ሰው ሰው እንደሚቀጥል ይደነግጋል። ስለዚህ መድን ሽፋኑ አብሮ ለገዢው ይተላለፋል ይላል። በርካታ የፍ/ቤት ክርክሮች አሉ። ባብዛኛው ግን የመድን ውሉ ይቋረጣል ከሚሉት የኢንሹራንስ ፖሊሲዎቹ ይልቅይቀጥላሉ የሚለው የንግድ ሕግ

673 (1) ያስገድዳል በሚል እስከ ሰበር ትርጉም ተሰጥቶባቸዋል። ይሁን እንጂ የገዢው መግዛቱን አለማሳወቁ መድን ሰጪውን ውሉን የማቋረጥ መብቱን እንዳይጠቀምበት አድርጓል። በንግድ ሕግ ቁጥር 673 (2) ላይ ንብረቱ የተላለፈለት ሰው እና ኢንሹራንስ ሰጪው ንብረቱ ከተላለፈበት ቀን አንስቶ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ውሉን ሊያፈርሱ እንደሚችሉ ተደንግጓል። በመሆኑም የገዢዎች አለማሳወቅ መድን ሰጪውን በዚህ ድንጋጌ (673 (1)) የተቀመጠውን መብቱን ዕንዳይጠቀምበት አድርጓል። ከዚህ በመነሳት አንዳንድ ድርጅቶች ለምሣሌ አባይ ኢንሹራንስ ገዢው ካላሳወቀ መድን ሰጪው ግዴታ የለበትም የሚል አንቀጽ በመድን ውሉ ውስጥ አስገብተዋል። ግን አባይ ኢንሹራንስም ቢሆን በቅርቡ በፍ/ቤት ተወስኖበታል። መድን ሰጪው የሥጋቱን መጠን ማስላት እንዳይችል የሚገድበው አሰራር ነው። ገዢው መግዛቱን ቢያሳውቅ ለምሳሌ በገዢው መንጃ ፈቃድ ቁጥሩ ብቻ ምን ያህል አደጋ እንዳደረሰ እና ምን ያህል ለአደጋ የተጋለጠ ሰው እንደሆነ ታይቶ መድን ሰጪውወይ ውሉ እንዲቀጥል አልፈልግም ሊል ወይም የተለያየ አረቦን ሊጠየቅ ይችላል። እንዲሁም የገዢው መኖሪያ ወሳኝ ሊሆን ይችላል። ለምሣሌ አዲስ አበባና ክልል ያለ ነዋሪ እኩል ስጋት አላቸው ለማለት አይቻልም ሲሉ አቶ ይነበብ አስረድተው በዚህ ነጥብ ጠጨማሪ ሀሳብ እንዲሰጡ ዕድሉን ለአቶ ፋሲል ሰጥተዋል።

<u>አቶ ፋሲል አለማየሁ</u>

ኢሹራብል ኢንተረስትን ተመዳኝ ጥቅም ብለን ተርጉመነው ነበር። በሰበር ፍ/ቤት ኮንትራክተሮች (ሥራ ተቋራጮች) በቦንዶች ኢንሹራብል ኢንተረስት (በመድን የሚሸፈን ጥቅም) የላቸውም በሚል የወሰኑበት አለ። ነጻ ተቋራጩ ለምሣሌ አንድ የግንባታ ሥራ ለመሥራት የውል ግዴታ ከገባ በኋላ ሥራውን በሚፈለገው ጥራትና እና ጊዜ ሰርቶ ባያስረክብ በአሰሪው ላይ የሚደርሰውን ጉዳት መድን ሰጪው በመድን ውሉ መሰረት ሊክስ ወይም መድን ሊሆን የሚገባው ግዴታ የኢንሹራንስ ቦንድ ተብሎ ሊጠራ የሚችል ሲሆን ሰበር ፍ/ቤት ነጻ ተቋራጩ በዚህ ውል ውስጥ በኢንሹራንስ የሚሸፈን ጥቅም የለውም በማለት ወስኗል። ነገር ግን አንድ ሰው በሌላ ላይ ያለው በገንዘብ የሚተመን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በመድን ሊሸፈን ይችላል። ለምሳሌ ተበድሮ የሚሠራ ባለሞያለአሰሪው መድን እንዲሆን ሲባል እንዲህ ዓይነት የመድን ውል ሊገባ ይችላል። ኮንትራክተርም ተመሣሣይ ውል ሊገባ ይችላል። ኃላፊነቱን ወደ ኢንሹራንስ ሊያስተላልፍ ይችላል። በግሌ በሰበር ውሳኔ አልስማማም። እንዲህ ዓይነት የገንዘብ ኃላፊነት የሚተላለፍባቸው ኢንሹራንሶች ቦንድ ኢንሹራንስ ይባላሉ። በሌሎች ሀገሮች የገንዘብ ሃላፊነቶች በግብይት ይተላለፋሉ። ኃላፊነቶቹ ደግሞ መድን ሲገባላቸው የበለጠ አስተማማኝነት ይኖራቸዋል። ሰበር

በሌላ ውሳኔ በአንድ በኩል ኢንሹራንስ ናቸው ካለ በኋላ መልሶ ግን ይርጋው የሚታየው በኢንሹራንስ ህግ ሳይሆን በፍትሐብሔር ሕጉ ነው ብሎ ወስኗል፡፡ አገም ጠቀምና እርስ በርሱ የሚጋጭ አይነት ነው፡፡

ሌላው መነሳት ያለበት የገንዘብ ዋስትና (ባንክ ጋራንቲ) ግን የመድን ውል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኢንሹራንስ የሚሰራው በክፍያ (በአረቦን) ነው፡፡ በባንክ ጋራንቲ ግን ባንኩ ጥቅሙን የሚያገኘው በወለድ ነው እንጂ በኢንሹራንስ አረቦን ክፍያ መልክ አይደለም፡፡ ብሔራዊ ባንክም ቢሆን ቦንድ በኢንሹራንስ እንዳይሰጥ የከለከለበት የራሱ የሆነ ምክንያት የነበረው ሲሆን ኢንሹራንስ አይደለም በሚል ግን አልነበረም፡፡

ሰበር ይህንን ቦንድ ኢንሹራንስ አይደለም የሚለውን ድምዳሜውን ለማጠናከር ሲል ስለጠለፋ ዋስ ያነሳውም አግባብነት የሌለው ነው፡፡

የቦንድ ኢንሹራንስ እኤአ ከ1971 በኋላ በአሜሪካ እየዳበረ መጣ፡፡ በእኛም ሀገር የመንግሥት መ/ቤቶች በቦንድ ከህዝብ የመበደር ስልጣን ስለነበራቸው እየዳበረ መጣ በማለት ስለ ኢንሹራብል ኢንተረስት (በመድን ሊሸፈኑ ስለሚችሉ ጥቅሞች) አስተያየታቸውን አክለዋል፡፡

<u>አቶ ይነበብ ደርሰህ</u>

2ኛው የመወያያ ነጥብ የኃላፊነት ኢንሹራንስ ነው፡፡ አንድ ሰው ከውል ውጪ በሚፈጽመው ጥፋት ምክንያት፣ ወይም የንብረት ባለቤት በመሆኑ ብቻ ያለጥፋት ወይም ስለሌላው ኃላፊ በመሆኑ ምክንያት የሚመጣበት ኃላፊነትን ይመለከታል፡፡ እንዲሁም ከውል አፈጻጸም ጋር በተያያዘ (ለምሣሌከማጓጓዣ፣ ከመጠበቅ፣ አገልግሎት ከመስጠት ወዘተ. ውል) የሚመነጭኃላፊነት አለ፡፡ በሥራ ውል ደግሞ አሠሪው በሠራተኞች ላይ በሚደርስ ጉዳት በአሰሪና ሠራተኛ አዋጁ መሠረት ኃላፊነት ሊመጣበት ይችላል፡፡ በንግድ ሕጉ ከቁ. 685 እስከ 688 ተደንግጓል፡፡ ተሽከርካሪን በተመለከተ ደግሞ አዋ ቁ 799/05 ወጥቷል፡፡

ከኀላፊነት ኢንሹራንስ ጋር በተያያዘ አንዱ ጥያቄ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ክሣው በቀጥታ በተጎጂው ሊጠየቅ ይችላል ወይ የሚለው ነው፡፡ ፍ/ቤቶች አይችልም በሚል ሲወስኑ ቆይተዋል፡፡ ለተሽከርካሪ ግን አዋ ቁ 799/2005ዓ.ም አንቀጽ 17/2 በተለየ ሁኔታ ይፈቅዳል፡፡ ስለዚህ አንድ ተሽከርካሪ

በሰው ላይ ጉዳት ቢያደርስ ተጎጂው የግድ የመድን ገቢው እስኪጠይቅለት መጠበቅ ሳያስፈልገው በቀጥታ መድን ሰጪውን በውሉ መሠረት ካሣ ክፈለኝ በማለት መጠየቅ ይችላል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ በሞተር ተሽከርካሪ ከሚደርስ ጉዳት በስተቀር በሌሎች ጉዳቶች ተጎጂው መድን ሰጪውን በቀጥታ መጠየቅ ስለማይችል ተጎጂው ክሱን መመሥረት የሚችለው ለጉዳቱ ኃላፊነት ባለበት መድን ገቢው ላይ ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ መድን ገቢው ሲከሰስ እሱም በበኩሉ መድን ሰጪው ወደ ክሱ ይግባልኝ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 መሠረት መጠየቅ ይችላል፡፡ ነገርግን መድን ሰጪው ወደ ጉዳዩ ከገባ በኋላ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት ለጉዳቱ ካሣ የመክፈል ወይም መድህን የመሆን ግዴታ የለብኝም በማለት ቢቃወምና በዚህ ረገድ በመድን ገቢውና ሰጪው መካከል የእርስ በእርስ ክርክር ቢነሳ በሁለቱ መካከል የተነሳው ክርክር በዚያው መዝገብ ዕልባል ሊያገኝ ይችላል አይችልም በሚለው ጭብጥ በፍ/ቤቶች ውስጥ ክርክር ሲነሳ ይስተዋላል፡፡ ይህንን በሚመለከትየሰበር ፍ/ቤት የመድን ሰጪው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 መሠረት ወደ ጉዳዩ ከገባ በኋላ በመድን ሰጪውና በመድን ገቢው መካከል መድን ውሉን መሠረት ያረገ ክርክር ቢነሳ መድን ሰጪው ከክርክሩ ሊወጣይገባል በሚል የተወሰነበት አለ፡፡ አግባብ አይመስለኝም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 (1) እስከገባ ድረስ ተጠቃልሎ ሊወሰን ይገባል እንጂ ሊወጣ አይገባም፡፡ የተባለውየሰበር ውሳኔ መዝገብን የሚያበዛ እና ክርክርን የሚያጓትት አሰራር ነው፡፡ ሁለተኛ ጉዳዩ አንድ ጊዜ ዳኝነት ቢያገኝ ለተጎጂውም የበለጠ ዋስትና የሚሰጠው እና ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ መድን ሰጪው ከጉዳዩ ከተሰናበተ በኋላ በመድን ገቢው ላይ ቢወሰንና በሌላ በኩል ደግሞ በሌላ መዝገብ መድን ሰጪው መድን የመሆን ግዴታ አለበት ተብሎ ቢወሰን እሱ በሌለበት በመድን ገቢው ላይ የተሰጠው ውሣኔ የራሱን የመድን ሰጪውን መብት የሚነካ ይሆናል፡፡ ከዚህም በላይ መድን ሰጪው ክርክሩን ሊመራው እንደሚችል በንግድ ህጉ ላይ የተቀመጠ በመሆኑ መድን ሰጪው ሊከራከር ይገባል፡፡

ሌላው ስለ ተሽከርካሪ የሚደነግገው አዋጅ ቁ 799/2005ዓ.ም በአንቀጽ 5 ና 6 ላይ መድን ሰጪዎች በተጎጂዎች ሲከሰሱጉዳቱ በፖሊሲ አይሸፈንም የሚል መቃወሚያ ክርክር በተጎጂዎች ላይ ማቅረብ እንደማይችሉ ደንግጓል፡፡ ነገርግን መድን ሰጪዎች ለተጎጂዎች ከፖሊሲው ውጪ የከፈሉትን ከመድን ገቢው ላይ መልሰው መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ማህበራዊ ቀውስን ለማቃለል ሲባል የተደነገገ አንቀጽ ነው፡፡ ደንበኞች ግን እንዴት ኢንሹራንስ ገብቼ መልሼ በመድን ሰጪው እጠየቃለሁ በሚል ግር ሲሉ ይታያል፡፡

3ኛ/ ስለ ሠራተኞች በተመለከተ አሰሪዎች በሥራ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት ያለባቸው እንደመሆኑ ኢንሹራንስ የሚገቡበት ሁኔታ አለ። ሆኖም ካሣው የሚከፈለው አደጋው በስራ ሰዓት ቁም ቦታ ሲደርስ ነው።

ስለ አካል ጉዳትና አደጋ የተደነገገው በንግድ ሕጉ ቁጥር 711 ና 712 ብቻ ነው። በኢንሹራንሱ ውስጥ በተወሰነው ጊዜ በኢንሹራንስ ገቢው ላይ አደጋና ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ካሳ ለራሱ ወይም ከሞተም ለተጠቃሚ የሚከፈልበት ነው።

የሕይወት ኢንሹራንስ እንደ ውርስ ሀብት ይቆጠራሉ። ግን ላለፉት 30 ዓመታት ክርክር አለ። ንህቁ 701 (1) ለኢንሹራንስ ገቢው ተጠቃሚን የመሰየም መብት ይሰጣል። ቢሆንም በተለይ የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁ.2 ሚስትና ልጆች ግን በኢንሹራንስ ውሉ ላይ ስማቸው ተለይቶ ባይጻፍም ተጠቃሚ መሆናቸውን ይደነግጋል።በሌላ በኩል ግን የፍትሀብሄሩ ሕግቁ 827(1) ሟቹ ተጠቃሚውን ያልወሰነ እንደሆነ በህይወት ኢንሹራንስ የሚከፈለው ገንዘብ የውርስ ንብረት ክፍል እንደሚሆን ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ንዑስ ቁ.2 ተቃራኒ ሁኔታ ሲኖር ግን የውርሱ ሀብት ክፍል አይሆንም ይላል። ይህ ማለት ማቹ የኢንሹራንስ ተጠቃሚዎቹን ወስኖ ከሆነ ግን የኢንሹራንስ ክፍያው የውርሱ ክፍል አይሆንም ወይም ለወራሾች አይሆንም ማለት ነው። ይህ ከላ ከተጠቀሰው የንግድ ሕግ ጋር በጣም ይጻረራል። በሌሎች ሀገሮችም የተለያዩ ሁኔታዎች አሉ። እንደጋራ ንብረት የሚቆጠርባቸው ሀገሮች አሉ። ምሣሌ አሜሪካ። ፕሪሚየሙ ከጋራ ንብረት ከተከፈለ ጥቅሙ የጋራ የሚሆንባቸው ሀገሮች አሉ። ስለዚህ 50 በመቶ የሚስት ይሆንና ሌሎች ተጠቃሚዎች 50 በመቶ ብቻ ያገኛሉ። ቀደም ባሉ የጠቅላይ ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲህ ዓይነት ውሣኔ ነበር። ይህ ውሳኔ በጣም ፍትሐዊ ነው። በተለይ ሌሎች ንብረቶች በሌሉበት ሁኔታ ተገቢነቱ አያጠያየቀቅም። ይህን አተረጓጎም ጥያቄ ውስጥ የሚከተው ለምሳሌ ባንክ ኢንሹራንስ ሲገባ ነው። ተበዳሪው የሞተ እንደሆነ ኪሳራ ለመቀነስ ሲል ባንክ በተበዳሪው ስም የሕይወት ኢንሹራንስ ሊገባ ይችላል። ስለዚህ ዘርዘር ያለ ድንጋጌ ይሻል። እንዲሁም አሰሪ ለሠራተኞች የህይወት ኢንሹራንስ በሚገባበት ጊዜ ተጠቃሚ ማን እንደሆነ ሳይገለጽ ሲቀር ሊደረግ የሚችለው ምንድነው የሚል ጥያቄም አለ። አንድ ፍ/ቤት ተጠቃሚ የለም በሚል ወደ ውርስ ሀብት ውስጥ ያስገባበት ውሣኔ አለ። የአንዳንድ ሀገሮች ፍ/ቤቶች በፍቺ ጊዜ ተጠቃሚን የመሰየም መብትን የሚገድቡ እና ለልጆች ኢንሹራንስ እንዲገባ የሚያዙ አሉ። ለምሳሌ ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ካሉ የሕጻናቱን ጥቅም ለማስከበር ሲሉ ህጻናቱ በተጠቃሚነት ስማቸው ተጽፎ ወላጆች የሕይወት ኢንሹራንስ እንዲገቡ የሚያዙ ፍ/ቤቶች አሉ። የጋራ ንብረት መብትን እና የልጆችን

ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ ህግ መኖር አለበት፡፡ አበዳሪ የራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚገዛቸው ኢንሹራንሶች ከዚህ ውጪ መሆን አለባቸው፡፡ ሸሪኮችም እንዲሁ፡፡ ከንግድ ውጪ ግን በተለይ በግለሰቡ የሚገባው ኢንሹራንስ ግን ገደብ ገደብ ሊኖረው ይገባል ሲሉ አስረድተው አወያዩ ቤቱ ሀሳብ እና ጥያቄ እንዲያቀርብ ውይይቱን ከፍተዋል፡፡

<u>ውይይት</u>

<u>አቶ ደረጀ አሰፋ</u>

በፍ/ሕ/ቁ 2143 (1) መሠረት ተጎጂው ጉዳቱ በደረሰ በ2 ዓመት ውስጥ ካልከሰሰ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፡፡ ነገር ግን ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ከሆነ እና የወንጀሉ የይርጋ ዘመን የሚረዝም ከሆነ ይርጋው በወንጀሉ የይርጋ ዘመን ልክ እንደሚራዘም በንዑስ ቁ. 2 ላይ ተደንግጓል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኮ/መ/ቁ 58920 የተፈጸመው ጥፋት በወንጀል የሚያስቀጣ ከሆነ ይርጋው በወንጀል ሕጉ ለወንጀል ድርጊቱ ክስ በተቀመጠው የይርጋ መጠን መታሰብ እንዳለበት ወስኗል፡፡ ነገር ግን ጉዳቱን ያደረሰው ያንድ መሥሪያቤት ሠራተኛ ለምሣሌ ሾፌር የሆነ እንደሆነ እና ነገር ግን በፍትሐብሔር የተከሰሰው መስሪያቤቱ ከሆነ ጉዳት አድራሽ ባልሆነው መቤት ላይ ለቀረበው ክስ የወንጀሉ ይርጋ አግባብነት አለው ወይ ብለዋል፡፡

<u>ሌላ ተሳታፊ</u>

1. የኢንሹራንስ ቦንድን በሚመለከት በመጀመሪያ ኢንሹራንስ እርግጠኛ ላልሆነ ነገር የሚገባ ነው፡፡ ቦንድ ግን የሚመለከተው የውል አፈጻጸምን እንጂ እርግጠኛ ያልሆነ አደጋን ባለመሆኑ የኢንሹንስ ውል ነው ለማለት ይቻላል ወይ፤
2. ሰበር ፍ/ቤት በመኪና ግጭት ጉዳት ሲደርስ ተጎጂው በቀጥታ ኢንሹራንሱን መክሰስ የሚችል ስለመሆን አለመሆኑ የሰጠው ውሳኔ አለ ወይ፤

<u>ሌላ ተወያይ</u>

ኃላፊነትን በተመለከተ ለምሳሌ በህብረት ኢንሹራንስ ውስጥ በጠበቆች ለሚደርስ የሙያ ጉዳት ሽፋን አለ ወይ፤ ህብረት ኢንሹራንስ ሽፋን ይሰጣል ወይ፤

**ሌላ ተወያይ**

ብድር ኢንሹራንስ የማይሆንበት ብዙ ምክንያቶች አሉ ሲሉ በአቶ ፋሲል ሀሳብ አልስማማም ብለዋል፡፡ ብድር መከፈል ያለበት ዕዳ እንጂ መድረሱ የሚያጠራጥር ጉዳት አይደለም የሚልና ሌሎች ነጥቦችን በማንሳት ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

**አቶ ከሁሉም ይበልጣል**

የኛ ሀገር ህግ ከአየር ንብረት ኢንሹራንስ ጋር በተያያዘ የሚለው አለ ወይ ሀሳብ ቢሠጥበት ብለዋል፡፡

**ሌላ ተወያይ**

ባንኮች ባበደሩት ብድር ላይ ኢንሹራንስ ሲገቡ ሊወሰንላቸው የሚገባው እስከምን ነው

ኮንሲኮንሻል ሎስ ወይም በጉዳት ምክንያት የታጣ ገቢ ሊጠየቅየሚችለው መቼ ነው

**አወያዩ**

ዛሬ የዓለም የመሬት ቀን መሆኑ ስለ አየር ንብረት ከተነሳው ጥያቄ ጋር ግጥምጥሞሹ እንደሚያስገርም አሰታውሰው ጽሁፍ አቅራቢዎቹ ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ እድል ሰጥተዋል፡፡

**ምላሽ**

**አቶ ይነበብ**

1. በሰራተኛ ለተደረሰ ጉዳት በአሰሪው ላይ ለሚቀርብ ክስ ይርጋው መታሰብ ያለበት እንዴት ነው ለሚለው አሰሪዎች አንድም ባለንብረት በመሆናቸው ስለሰራተኛቸው ጥፋት ይጠየቃሉ፡፡ ስለሌላው ሰው ኃላፊ ሆነው ሲጠየቁ ኃላፊነቱ የሚመነጨው ከሠራተኛው ጥፋት በመሆኑ 2143/2/ ን መጠቀም አለብን፤ ማለትም የወንጀሉ ረጅም የይርጋ ዘመን ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡፡፡ በወንጀል ተከሶ መቀጣት አለመቀጣት ሌላ ጉዳይ ሆኖ ግን የሚያስጠይቅ እስከሆነ ድረስ ይርጋው በንዑስ 2 እንደሚታሰብ ሰበር ወስኗል ብለዋል፡፡

2. በመኪና ተጎጂዎች አማካኝነት በኢንሹራንስ ሰጪዎች ላይ የቀረቡ ክሶችን በሚመለከት ሰበር በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 43 (1) መሠረት ኢንሹራንሶቹ ወደ ክሱ እንዲገቡ ካልተጠየቀ በቀር መድን ሰጪዎች በቀጥታ ሊጠይቋቸው አይችሉም ብሎ ወስኗል፡፡ ለተሸከርካሪዎች ግን ተጎጂዎቹ ኢንሹራንሶቹን በቀጥታ መጠየቅ እንደሚችሉ በኣዋጅ ቁ 499/2005ዓ.ም በአንቀጽ 17 ላይ ስለተቀመጠ የሰበር ውሳኔም ቢሆን ተገቢነት የለውም፣ በሰበርም ሊሻሻል ይገባል ባይ ነኝ፡፡ ሰበር አዋጁን ከናካቴውም አልጠቀሰውም፣ ብለዋል፡፡

3. ስለ ፋይናንሻል ጋራንቲአቶ ፋሲል ሲመልሱ ክሬዲት (የብድር) ኢንሹራንስ አንሰርኒቲን (አጠራጣሪነትን) አያሟላም በተባለው አልስማማም፡፡ ሞት ለምሳሌ ቀኑ አይታወቅም እንጂ ርግጥ ነው፡፡ ሥጋት ያላቸውን ሰዎች በማሰባሰብ እና በዕድል ሕግ መሠረት የሚሠራ ንግድ ነው፡፡ ግን ብድርን ስንመለከት ብዙ ሊሰባሰቡ የሚችሉ ሰዎች ስለሌሉ ሪስኩን (ኃላፊነቱን) ከፍ ያረገዋል፡፡ ያ ስለሆነ ወደ ኮላተራል ይገባል፡፡ ኢንሹራንስ የሚፈልጋቸው ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው ተነሳ መድን ገቢዎቹ ተከሰው የተከፈለላቸውን ይከፍላሉ፡፡

እንዲሁም ካልከፈለ እከፍላለሁ አሉ እንጂ አላበደሩም፡፡ የባንክ ሥራ ነው ሊባልም አይችልም፤ አይገባምም፡፡ ኢንሹራንሶች ፎር ክሎዠር ሥልጣን የሌላቸው መሆኑ ችግር ከሆነ ለምን ለመድን ሰጪዎችም ይህ ሥልጣን አይሰጥም፤ ይህ መድን አይደለም ለማለት የሚበቃ ምክንያት አይደለም፡፡ አሜሪካ ውስጥ 9 ትልልቅ ብድርን መድን ዋስትና የሚሰጡ ኩባንያዎች አሉ፡፤ ንግዱ ግን አዲስ ነው፡፡ ሙሉ ለሙሉ ከመከልከል ይልቅ መረጃ እንዲለዋወጡ በመፍቀድ፣ ፎርክሎዠር ሥልጣን በመስጠት ወዘተ ማስተካከል ይቻል ነበር፡፡ ለጊዜው መከልከሉ ተገቢ ነበር፡፡ እሱን ለመጠበቅ ነው፡፡ የተከለከሉት ግን ኢንሹራንስ አይደሉም በሚል አይደለም፡፡

ባንኩም ኮነትራክተሩም ኢንሹራብል ኢንተረስት አላቸው፡፡ ባንኩ ያልተከፈለው እንደሆነ የሚያጣው ተመዳኝ የሆነ ጥቅም አለው፡፡ ኮንትራክተሩም በተለያዩ ምክንያቶች በቶሎ ባለማጠናቀቅ ወይም ተጨማሪ በማውጣት ለሚደርስበት ጉዳት መድን ውል ሊገባ ይቻላል፡፡ በብዛት ግን የሚታየው ባንኩ ሲዋዋል ነው፡፡ ሁለቱም ግን ህጋዊ ሊመደን የሚችል ጥቅም አላቸው ብለዋል፡፡

4. ኢንሹራብል ኢንተረስት የነበረ መሆን አለመሆኑየሚመዘነው ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ የነበረውን ሁኔታ በማመዛዘን ነው፡፡ እርግጥ በሚገባበት ጊዜ ይታያል፡፡

5. ኮንሲኩዌንሻል ሊገዛለት የሚችል አንድ ስጋት ነው። በተረፈ ግን ሊከፈል አይገባም። ግን ካሳ በማዘግየታቸው የሚደርስን ሊከፍሉ ይገባል፤ ሰበርም ወስኗል። በመርህ የሚከፈለው ሽፋን ላለው ነው።
6. ለጠበቆች መግባት ይቻላል። ሕብረት ብቻ ሳይሆን ሁሉም ከተጠየቁ ይሰጣሉ።
7. ካተስትሮፊስ በመርህ አይሸፈኑም። ግን በልዩ ሁኔታ ሊሸፈኑ ይችላል። ብዙ ጊዜ ግን እንዲህ ዓይነቶች የሚሸፈኑት በመግሥት ነው። ምክንያቱም ይህ የተፈጥሮ አደጋ ጉዳቱ ከፍተኛ ስለሆነ የግል ኢንሹራንስ ኩባንያዎችን ጠራርጎ ሊያጠፋቸው ስለሚችል ነው።
8. ኢንሹራንሶች ሊጠየቁ የሚገባው በብድሩ ወይም በቀረው ንብረት መጠን ነው። ከዚህ በላይ የተሰጡ ውሳኔዎች አሉ። አግባብ አይደለም። ኢንሹራብል ኢንተረስቱም በዛው መጠን ነው።

### አቶ ቴዎድሮስ ምህረት (የማህበሩ ፕሬዚዳንት)

ውይይቱ ሰፊ በመሆኑ ሁሉንም ነገሮች መነካካት አስቸጋሪ መሆኑን ገልጸው አመስግነው ከቀኑ 6፡30 አብቅቷል።